የኦሪገን የስራ አጥነት መድን የጥቅማጥቅሞች ማመልከቻ

ይህ ቅጽ የFrances Online (frances.oregon.gov) እና የUI የመገናኛ ማዕከል (UI Contact Center) (877-345-3484) አማራጭ ነው። Frances Online መጠቀም ወይም መደወል ካልቻሉ ብቻ ይህን ቅጽ ይጠቀሙ።

የክፍያ ጠያቂ ምዝገባ

መጠርያ ስም፡	የአያት ስም፡	የአባት ስም፡
የአሁኑ ወይም የቀድሞ አሰሪዎ/ችዎ በሌላ ስም የሚያውቅዎ ከሆነ፣ እባክዎ ያንን ስም ያስገቡ፡		
የትውልድ ቀን፡	የዩናይትድ ስቴትስ ዜጋ ነዎት? ☐ አዎ ☐ አይ	
እንዲሰሩ ተፈቅዶልዎታል? ☐ አዎ ☐ አይ "አዎ" ካሉ፣ የስራ ፈቃድ ሰነዶችን ቅጂዎች ከማመልከቻ ጋር ያካትቱ።		
የመንጃ ፈቃድ ቁጥር እና ግዛት፡	የኢሜይል አድራሻ፡	

የማንነት መለያ/መታወቂያ

ማስታወሻ፡ ማንነትዎን ለማረጋገጥ የማህበራዊ ዋስትና ቁጥርዎን ማስገባት አለብዎት። የግል መረጃዎን መጠበቅ ለኛ አስፈላጊ ነው። ሁሉንም የማህበራዊ ዋስትና ቁጥሮች ከማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር ጋር በኮምፒዩተር በማጣጣም ወይም በማመሳከር እናረጋግጣቸዋለን። ይህ ማመሳከርያ የተሳካ ካልሆነ፣ የስራ አጥ የመድን ዋስትና ማመልከቻዎ ሊጠናቀቅ ወይም ሊሟላ አይችልም። በሐገር ውስጥ ገቢ ሕግ (Internal Revenue Code) እና በኦሬጎን አስተዳደራዊ ደንቦች (Oregon Administrative Rules) መሰረት የሥራ አጥ ዋስትና ካሳ እንዲከፈልዎ በሚጠይቁበት ጊዜ የማህበራዊ ዋስትና ቁጥርዎን መስጠት ወይም ማሳወቅ አለብዎት። የማህበራዊ ዋስትና ቁጥርዎ ያገኙትን ጥቅማ ጥቅም ግብር እንደሚከፈልበት ገቢ ለሀገር ውስጥ ገቢ አግልግሎት (Internal Revenue Service) እና ለኦሬጎን ገቢዎች መምሪያ (Oregon Department of Revenue) ሪፖርት ለማድረግ ጥቅም ላይ ይውላል። ቁጥሩ ለማንነት ማረጋገጫ ለማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር ይላካል። በተጨማሪም ቁጥሩ ያቀረቡትን የክፍያ ጥያቄ ለማስኬድ፣ ለስታትስቲካዊ ተግባር፣ በኤሌክትሮኒክ የስራ ማጣጣሚያ ስርዓት ውስጥ እርስዎን ለመመዝገብ እንደ ምዝገባ የሚያገለግል ሲሆን ለOne-Stop አገልግሎቶች ለWorkSource Partners ይጋራል። ቁጥሩ ለግዛት ኤጀንሲ የእዳ አሰባሰብ ተግባራት ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል ሲሆን ለጥቅማ ጥቅም ክፍያዎ ReliaCard®ን ከመረጡ ReliaCard® VISA ካርድ እንዲሰጥዎ ለU.S. Bank ሊላክ ይችላል።

የማህበራዊ ዋስትና ቁጥር፡

የመጀመርያ የክፍያ መረጃ

በዚህ ማመልከቻ ላይ እውነቱን መናገር አለብዎት።

እርስዎ የሚሰጡት መረጃ ከስራ አጥ የመድን ዋስትና ፕሮግራም ለሚሰጡት ጥቅማ ጥቅሞች እርስዎ ብቁ መሆንዎን ለመወሰን ጥቅም ላይ ይውላል። እርስዎ በማመልከቻዎ ላይ እውነተኛውን እና ትክክለኛውን መረጃ መስጠትዎ በጣም አስፈላጊ ነው። ሆነ ብለው የሀሰት መረጃ ከሰጡ ወይም ጥቅማ ጥቅም ማግኘት እንዲችሉ አስበውበት እውነተኛውን እና ትክክለኛውን መረጃ ሳይሰጡ ቢቀሩ ተጨማሪ ቅጣቶች ሊጣሉብዎት ይችላሉ። ለሁሉም ጥያቄዎች መልስ ሳይሰጡ ቢቀሩ ማመልካቾዎ የሚታይበትን ሂደት እንዲዘገይ ሊያደርገው ወይም ማመልከቻው ተመልሶ ወደርሶ በፖስታ እንዲላክ ሊያስደርግ ይችላል።

የአድራሻ መረጃ

የፖስታ መልእክት መቀበያ አድራሻ፡		ከተማ፡
ግዛት፡	ዚፕ ኮድ:	☐ የመኖርያ አድራሻዎ ከፖስታ መልእክት አድራሻዎ ጋር አንድ ከሆነ፣ እዚህ ጋ ምልክት ያድርጉ።
የመኖሪያ አድራሻ:	ከተማ:	ግዛት:
ዚፕ ኮድ:	ስልክ ቁጥር:	የመልእክት ስልክ ቁጥር:
የፖስታ መቀበያ አማራጭ፡ የፖስታ መቀበያ አማራጮችዎ መልእክት የሚቀበሉበትን ሁኔታ እና የቋንቋ ምርጫዎ ምን እንደሆነ ይወስናል። ምርጫዎችዎን በማናቸውም ጊዜ በሚከተለው መለወጥ ይችላሉ frances.oregon.gov.		☐ ወረቀት ☐ ኤሌክትሮኒክ
የኛን አገልግሎቶች ለመረዳት ከእንግሊዘኛ ውጪ በሆነ ሌላ ቋንቋ መረጃ ማግኘት ይፈልጋሉ?		☐ አዎ ☐ አይ
"አዎ" ካሉ፣ እባክዎ የርስዎን ተቀዳሚ ቋንቋ ይጥቀሱ፡		

እባክዎ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይመልሱ

ባለፉት 12 ወራት ውስጥ፣ ከኦሬጎን ውጪ በሆነ በማናቸውም ሌላ ግዛት የጥቅማ ጥቅም ክፍያ ጥያቄ አቅርበው ነበር? ☐ አዎ ☐ አይ

በአሁኑ ወቅት እርስዎ በአካል የሚኖሩበትን ግዛት ያስገቡ፡

በአሁኑ ወቅት ወይም በሚቀጥሉት 12 ወራት ውስጥ (ከማህበራዊ ዋስትና ሌላ) የጡረታ ክፍያ እያገኙ ነው ይም ያገኛሉ? ☐ አዎ ☐ አይ

በማህበርዎ የቅጥር አዳራሽ በኩል ስራ እንዲፈልጉ የሚፈቅድልዎ ወይም በማህበሩ አሰሪዎች ዘንድ ብቻ ስራ እንዲፈልጉ ገደብ የሚያደርግብዎ የስምሪት ማህበር አባል ነዎት? ☐ አዎ ☐ አይ

የስምሪት ማህበር አባል ከሆኑ፣ የማህበርዎ ስምና ቁጥር ምንድን ነው?

ባለፉት 18 ወራት ውስጥ: ኦሬጎን ውስጥ ሲሰሩ ነበር? ☐ አዎ ☐ አይ ከኦሬጎን ግዛት ውጪ ሰርተው ነበር? ☐ አዎ ☐ አይ

በናሽናል ጋርድ ወይም በተጠባባቂ አሀድ ከሚሰጠው ስልጠና ውጪ፣ የ180 ቀናት ወይም ከዚያ በላይ ለሆነ ጊዜ ማናቸውንም ወታደራዊ አገልግሎት ፈጽመዋል? ☐ አዎ ☐ አይ

ማስታወሻ፡ የርስዎን DD-214 አባል 2፣ 3 ወይም 4 ቅጂ ማያያዝ ይችላሉ። ይህ አማራጭ ነው። ይሁን እንጂ የርስዎን ንጹህ እና ያልተቀየረ DD-214 ማያያዝ በክፍያ ጥያቄዎ ላይ የወታደራዊ አገልግሎት ደመወዞች በፍጥነት እንድንደምርበት ሊፈቅድልን ይችላል።

የU.S. Merchant Marine ማሪነር ሆነው ሰርተዋል? ☐ አዎ ☐ አይ

ተቀዳሚ ስራ

የርስዎ ተቀዳሚ ስራ ምንድን ነው?

በአሁኑ ወቅት የዚህ አይነቱን ስራ እየፈለጉ እና ለመቀበል ፈቃደኛ ነዎት? ☐ አዎ ☐ አይ

“አይ” ካሉ፣ እባክዎ ምክንያቱን ይግለጹ እና እርስዎ በአሁኑ ወቅት በትክክል እየፈለጉ ያለው የስራ አይነት ይጥቀሱ። “ማናቸውንም” ብለው አይጻፉ።

የብቁነት ጥያቄዎች

ማስታወሻ፡ ለሚሰጡ ጥቅማ ጥቅሞች ብቁ ሆነው ለመገኘት የሙሉ ሰዓትም ሆነ የትርፍ ሰዓት ስራ ሁለቱንም ለመቀበል ፈቃደኛ እና መገኘት የሚችሉ መሆን ይኖርብዎታል።

የሙሉ ሰዓት እና የትርፍ ሰዓት ስራ ለመስራት ፈቃደኛ ነዎት? ☐ አዎ ☐ አይ

"አይ" ካሉ፣ እባክዎ ምክንያቱን ይግለጹ፡

ማስታወሻ፡ ለሚሰጡ ጥቅማ ጥቅሞች ብቁ ሆነው ለመገኘት እርስዎ ለመስራት ፈቃደኛ እና እርስዎ ለሚፈልጉት የስራ ዓይነት የተለመዱ በሆኑ በሁሉም ቀናት እና ሰዓታት ለስራ መገኘት መቻል ይኖርብዎታል።

ለሰራው ዓይነት መደበኛ በሆኑ በሁሉም ቀናት ስና ሰዓት ለመስራት ፈቃደኛ ነዎት? ☐ አዎ ☐ አይ

"አይ" ካሉ፣ እባክዎ ምክንያቱን ይግለጹ፡

ተቀዳሚ በሆነው ስራዎ ላይ ለመጨረሻ ጊዜ ሲሰሩ በነበረበት ጊዜ ይከፈለዎት የነበረው ደመወዝ/ምንዳ ስንት ነበር? $ በ

ወደፊት ለሚያገኙት ስራ ይህንኑ የክፍያ መጣኔ ለመቀበል ፈቃደኛ ነዎት? ☐ አዎ ☐ አይ

"አይ" ካሉ፣ እባክዎ ምክንያቱን ይግለጹ እና እርስዎ ለመቀበል ፈቃደኛ የሚሆኑበትን አነስተኛውን የክፍያ መጣኔ ያስገቡ፡

እርስዎ በአሁኑ ወቅት የሙሉ ሰዓት ስራ መጀመር የማይችሉበት ማናቸውም ምክንያት አለ? *(ለምሳሌ፡ የግል ስራ፣ የመቋሰል አደጋ፣ ህመም፣ የልጆች ክብካቤ፣ መጓጓዣ፣ ወዘተ.)* ☐ አዎ ☐ አይ

"አዎ" ካሉ፣ እባክዎ ምክንያቱን ይግለጹ፡

ለመጨረሻ ጊዜ ስራ ከሰሩበት ቀን ጀምሮ ማናቸውንም ስራ አልቀበልም ብለው ነበር? ☐ አዎ ☐ አይ
"አዎ" ካሉ፣ እባክዎ ምክንያቱን ይግለጹ፡
እየተማሩ ነው? ☐ አይ ☐ ሙሉ ጊዜ ☐ ትርፍ ሰዓት ሙሉ ጊዜ ወይም ትርፍ ጊዜ ብለው ከመለሱ፣ ትምህርት ቤትዎ ለረጅም ጊዜ የስራ እድል አማራጮች የተግባር ልምምድ ስልጠና ወይም የስራ ክህሎቶችዎን ለማሻሻል የሚያግዝ ትምህርት ይሰጣል?
ባለፉት 18 ወራት ውስጥ፣ ከአንድ በላይ ለሆነ አሰሪ ሰርተው ነበር? ☐ አዎ ☐ አይ
የግል ስራ እየሰሩ ነው? ☐ አዎ ☐ አይ
ባለፉት 18 ወራት ውስጥ ባለሙያ አትሌት ሆነው ሰርተው ነበር? ☐ አዎ ☐ አይ
በአሁኑ ወቅት ተቀጥረው እየሰሩ ነው? ☐ አዎ ☐ አይ
ባለፉት 18 ወራት ውስጥ በማናቸውም የአንድ ሩብ ዓመት ጊዜ ውስ ሰፊውን ጊዜ በህመም ወይም በመቁሰል ምክንያት ማናቸውንም ዓይነት ስራ መስራት የማይችሉ ሆነው ነበር? ☐ አዎ ☐ አይ
በU.S. Armed Forces ውስጥ አገልግለው ያውቃሉ? ☐ አዎ ☐ አይ

የአሰሪ መረጃ በሚቀጥለው ገጽ ላይ ይጀምራል።

የአሰሪ መረጃ

ተጨማሪ አሰሪዎችን ለመዘርዘር፣ ይህን ገጽ በኮፒ አባዝተው ከዚህ ማመልከቻ ጋር ያያይዙት። ይህ መረጃ ከአሰሪዎ/ዎችዎ ጋ ይጣራል። በተጨማሪም ባለፉት 18 ወራት ውስጥ እርስዎ ለሰሩባቸው ለሁሉም አሰሪዎች ይገለጻል።

ማስታወሻ: የግል ስራ የሚሰሩ ከሆነ፣ አሰሪዎን "የግል ስራ" ብለው ይግለጹ።

አሰሪ #1:	በጣም የቅርብ ጊዜ የሆነው አሰሪ ስም:	
ስራ የጀመሩበት ቀን:		የመጨረሻ የስራ ቀን:
ያለፉት 18 ወራት የአጠቃላይ ገቢ ድምር ወይም ግምታዊ መጠን:		
ባለፉት ሁለት ዓመታት ውስጥ ከኦሬጎን ውጪ በሆነ ሌላ ግዛት ውስጥ ለዚህ አሰሪ ሰርተው ነበር?		□ አዎ □ አይ
ይህ አሰሪ የፌደራል መንግስት ኤጀንሲ ነው?		□ አዎ □ አይ
("አይ" ካሉ፣ ከዚህ በታች ወዳለው ወደ "አሰሪ የፖስታ አድራሻ" ይሂዱ) የመጨረሻው የስራ ቦታዎ ዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ነበር?		□ አዎ □ አይ
የመጨረሻው ህጋዊ የስራ ቦታዊ በየትኛው ግዛት ውስጥ ነበር? _____		
ለፌደራል መንግስት ለመጨረሻ ጊዜ ከሰሩበት ጀምሮ በሚኖሩበት ግዛት ውስጥ ለሌላ አሰሪ ሰርተው ነበር?		□ አዎ □ አይ
የአሰሪ የፖስታ አድራሻ:	የጎዳና አድራሻ መስመር 1:	
የጎዳና አድራሻ መስመር 2:		
ከተማ:	ግዛት:	ዚፕ:
□ የፖስታ አድራሻው ከሚሰሩበት አድራሻ ጋር አንድ ከሆነ እዚህ ጋ ምልክት ያድርጉ:		
የሚሰሩበት አድራሻ:	የጎዳና አድራሻ መስመር 1:	
የጎዳና አድራሻ መስመር 2:		
ከተማ:	ግዛት:	ዚፕ:
የአሰሪ ስልክ ቁጥር:	የስራ መደቡ መጠርያ:	
የስራ ግዴታዎች:		
የመጨረሻው የክፍያ መጣኔ: $ በ	አሁንም ለዚህ ለዚህ አሰሪ እየሰሩ ነው? □ አዎ □ አይ	
አይ ካሉ፣ ለዚህ አሰሪ መስራት ያቆሙት ለምንድን ነው? □ ተሰናበትኩ ወይም ተባረርኩ □ በፈቃደኝነት ለቀቅኩ □ በስራ ማነስ ምክንያት ተቀነስኩ □ ታገድኩ □ በስራ ማነስ ምክንያት ለጊዜው ተቀነስኩ		
ለጊዜው ስራ አጥ ከሆኑ፣ወደ ሙሉ ሰዓት ስራ መች እመለሳለሁ ብለው ይጠብቃሉ?		

አሰሪ #2:	በጣም የቅርብ ጊዜ የሆነው አሰሪ ስም፡	
ስራ የጀመሩበት ቀን፡		የመጨረሻ የስራ ቀን:
ያለፉት 18 ወራት የአጠቃላይ ገቢ ድምር ወይም ግምታዊ መጠን፡		
ባለፉት ሁለት ዓመታት ውስጥ ከኦሬጎን ውጪ በሆነ ሌላ ግዛት ውስጥ ለዚህ አሰሪ ሰርተው ነበር		□ አዎ □ አይ
ይህ አሰሪ የፌደራል መንግስት ኤጀንሲ ነው?		□ አዎ □ አይ
የአሰሪ የፖስታ አድራሻ፡	የጎዳና አድራሻ መስመር 1:	
የጎዳና አድራሻ መስመር 2:		
ከተማ:	ግዛት:	ዚፕ:
□ የፖስታ አድራሻው ከሰሩበት አድራሻ ጋር አንድ ከሆነ እዚህ ጋ ምልክት ያድርጉ:		
የሰሩበት ቦታ አድራሻ፡	የጎዳና አድራሻ መስመር:	
ከተማ:	ግዛት:	ዚፕ:
የአሰሪ ስልክ ቁጥር:	የስራ መደቡ መጠርያ:	
የስራ ግዴታዎች:		
የመጨረሻ የክፍያ መጣኔ: $ በ		አሁንም ለዚህ አሰሪ እየሰሩ ነው? □ አዎ □ አይ
አይ ካሉ፣ ለዚህ አሰሪ መስራት ያቆሙት ለምንድን ነው? □ ተሰናበትኩ ወይም ተባረርኩ □ በፈቃደኝነት ለቀቅኩ □ በስራ ማነስ ምክንያት ተቀነስኩ □ ታገድኩ □ በስራ ማነስ ምክንያት ለጊዜው ተቀነስኩ		
ለጊዜው ስራ አጥ ከሆኑ፣ወደ ሙሉ ሰዓት ስራ መች እመለሳለሁ ብለው ይጠብቃሉ?		

አሰሪ #3:	በጣም የቅርብ ጊዜ የሆነው አሰሪ ስም:	
ስራ የጀመሩበት ቀን፡		የመጨረሻ የስራ ቀን:
ያለፉት 18 ወራት የአጠቃላይ ገቢ ድምር ወይም ግምታዊ መጠን፡		
ባለፉት ሁለት ዓመታት ውስጥ ከኦሬጎን ውጪ በሆነ ሌላ ግዛት ውስጥ ለዚህ አሰሪ ሰርተው ነበር?		□ አዎ □ አይ
ይህ አሰሪ የፌደራል መንግስት ኤጀንሲ ነው?		□ አዎ □ አይ
የአሰሪ የፖስታ አድራሻ:	የጎዳና አድራሻ መስመር 1:	
የጎዳና አድራሻ መስመር 2:		
ከተማ:	ግዛት:	ዚፕ:
□ የፖስታ አድራሻው ከሰሩበት አድራሻ ጋር አንድ ከሆነ እዚህ ጋ ምልክት ያድርጉ:		
የሰሩበት ቦታ አድራሻ:	የጎዳና አድራሻ መስመር:	
ከተማ:	ግዛት:	ዚፕ:
የአሰሪ ስልክ ቁጥር:	የሥራ መደቡ መጠርያ:	
የስራ ግዴታዎች:		
የመጨረሻ ክፍያ መጣኔ: $ በ		አሁንም ለዚህ አሰሪ እየሰሩ ነው? □ አዎ □ አይ
አይ ካሉ፣ ለዚህ አሰሪ መስራት ያቆሙት ለምንድን ነው? □ ተሰናበትኩ ወይም ተባረርኩ □ በፈቃደኝነት ለቀቅኩ □ በስራ ማነስ ምክንያት ተቀነስኩ □ ታገድኩ □ በስራ ማነስ ምክንያት ለጊዜው ተቀነስኩ		
ለጊዜው ስራ አጥ ከሆኑ፣ወደ ሙሉ ሰዓት ስራ መች እመለሳለሁ ብለው ይጠብቃሉ?		

ታክስ ቀንሶ ማስቀረት

ታክስ ቀንሶ የማስቀረት ፈቃድ

እርስዎ የሚያገኟቸው ማናቸውም የስራ አጥ የመድን ዋስትና ጥቅማ ጥቅሞች የግብር ተመላሽ ጥያቄ ማቅረብ የሚያስፈልግዎ ከሆነ ሙሉ በሙሉ ግብር የሚከፈልበት ገቢ ነው። ግምታዊ የግብር ክፍያዎችን መጠን ማስቀመጥ ሊኖርብዎት ይችላል። ግምታዊ የግብር ክፍያዎችን መጠን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ ከሀገር ውስጥ ገቢ አገልግሎት ጋር ይገናኙ። ለግዛት የግብር መረጃ፣ ከኦሬጎን ገቢዎች መምሪያ ጋር ይገናኙ። ለፌዴራል ግብሮች የጥቅማ ጥቅምዎን 10% እና/ወይም ለግዛት ግብሮች 6% ተቀንሶ እንዲያዝ ሊመርጡ ይችላሉ።

ወደፊት በሚፈጸሙልዎት ክፍያዎች ላይ ታክሶ ቀንሶ ማስቀረትን በምን መልኩ እንድናከናውነው ይፈልጋሉ? እባክዎ አንዱን ይምረጡ።

☐ ከጥቅማ ጥቅም ክፍያዎቼ ላይ የፌዴራል 10% እና የግዛት የግል ገቢ ግብር 6% ሁለቱም ተቀንሶ እንዲያዝ አፈልጋለሁ።

☐ ለፌዴራል ገብ ግብሮች ከጥቅማ ጥቅም ክፍያዎቼ 10% ብቻ ተቀንሶ እንዲያዝ አፈልጋለሁ።

☐ ለግዛት የግል ገቢ ግብሮች ከጥቅማ ጥቅም ክፍያዎቼ 6% ብቻ ተቀንሶ እንዲያዝ አፈልጋለሁ።

☐ ከጥቅማ ጥቅም ክፍያዎቼ ላይ ግብር ተቀንሶ እንዲያዝ አልፈልግም።

የኦሬጎን የስራ መምሪያ ማረጋገጫው መሻሩን የሚገልጽ የጽሁፍ ማሳወቂያ ከእርስዎ እስከሚደርሰው ድረስ ይህ ማረጋገጫ ለዚህ ክፍያ ተፈጻሚ ሆኖ ይቆያል።

ጥቅማ ጥቅመዎን መቀበል

ጥቅማ ጥቅምዎ ከተፈቀደልዎት የጥቅማ ጥቅም ክፍያዎን መቀበል የሚፈልጉት እንዴት ነው? ጥቅማ ጥቅምዎን ለመላክ ቀጥታ ተቀማጭን መጠቀም የማንችል ከሆነ፣ የጠባበቂያ ክፍያ ዘዴው ያ ስለሆነ በዚህ ሰነድ መጨረሻ የሚገኘውን የU.S. Bank ReliaCard® ስምምነትን የግድ ማንበብ አለብዎት።

ማመልከቻዎ ከታየ በኋላ ReliaCard እንልክልዎታለን። ቀጥታ ተቀማጭ እንዲሆንልዎ መፈረም የሚፈልጉ ከሆነ፣ እባክዎ ከዚህ በታች ያለውን ጥያቄ ይሙሉ።

☐ ቀጥታ ተቀማጭ

☐ ዴቢት ካርድ (ReliaCard®)

የባንክ ሂሳብ መረጃ:

የራውቲንግ ቁጥር: _____

የሂሳብ ቁጥር: _____

እባክዎ ከዚህ ጋር የተያያዘውን የReliaCard® ስምምነት እና የዝርዝር እና መረጃ መግለጫውን ይመልከቱ።

አማራጭ መነሻ ዓመት

ለስራ አጥ የመድን ዋስትና ክፍያ ብቁ ለመሆን፣ በመነሻዎ ዓመት ውስጥ በቂ ደመወዞች እና ሰዓት ሊኖርዎት ይገባል። መደበኛው መነሻ ዓመት የክፍያ ጥያቄዎን ባቀረቡበት ቀን ያበቁት ከመጨረሻ አምስት ሩብ አመታት የመጀመርያዎቹ አራቱ ናቸው።

ኦሬጎን ውስጥ ወይም በመነሻው ዓመት ውስጥ ይሰሩ በነበረበት ሌላ ግዛት ውስጥ ለመደበኛ የመነሻ ዓመት ክፍያ ብቁ ካልሆኑ፣ የክፍያ ጥያቄዎ ይበልጥ የቅርብ ጊዜ የሆኑትን ደመወዞች በመጠቀም በድጋሚ የሚወሰን ሲሆን የኦሬጎን አማራጭ የመነሻ ዓመት ክፍያ እናቀርባለን።

አማራጩ የመነሻ ዓመት የክፍያ ጥያቄ እርስዎ የክፍያ ጥያቄዎን ባቀረቡበት ቀን በተጠናቀቁት የመጨረሻ አራት ሩብ አመቶች ውስጥ ያሉ ደመወዞችን እና ሰዓቶችን ይጠቀማል። ስለአማራጭ የመነሻ አመት የክፍያ ጥያቄዎች መረጃ፡

መደበኛውን የመነሻ ዓመት በመጠቀም ብቁ ከሆኑ፣ አማራጭ የመነሻ ዓመት የክፍያ ጥያቄ ለማቅረብ ብቁ አይደሉም። ማናቸውም ሊኖሩ የሚችሉ የጎደሉ ደመወዞች ካሉ ፍለጋ እና ማጣራት እናደርጋለን። በመደበኛው መነሻ ዓመት ውስጥ ተጨማሪ ደመወዞች እና ሰዓታት በኋላ ላይ ካገኘን፣ አማራጭ የመነሻ ዓመት ክፍያዎን ወደመደበኛ የመነሻ ዓመት እንቀይራለን። ይህም በሚያገኙት የጥቅማ ጥቅም መጠን ላይ ለውጥ ሊፈጥር ይችላል።

ለአማራጭ የመነሻ ዓመት ክፍያ፣ ከክፍያ ጥያቄዎ ላይ ከደመወዞችዎ እና ሰዓቶችዎ የድሮውን ሩብ ውድቅ አድርገነ በጣም በቅርብ ጊዜ የተጠናቀቀውን የደመወዝና ሰዓት ሩብ እንደምራለን።

አሁን አማራጭ የመነሻ ዓመት ክፍያ ጥያቄ ካቀረቡ፣ ወደፊት በሚያቀርቡት በማናቸውም የክፍያ ጥያቄ ላይ ይህን አዲሱን የደመወዝ ሩብ ደግመው መጠቀም አይችሉም። በኋላ የሚቀርብ የክፍያ ጥያቄ በሶስት የደመወዝ እና ሰዓታት ሩብ ዓመታት ላይ ብቻ ሊመሰረት ይችላል።

በፈቃደኝነት ማሳወቅ

በዚህ ክፍል የሚሰጧቸው መልሶች ስለክፍያ ጥያቄዎ ውሳኔዎች ለመወሰን ጥቅም ላይ አይውሉም። የምናገለግላቸውን የተለያዩ ማህበረሰባት በተሻለ ሁኔታ እንድረዳ ያግዘን ዘንድ፣ ከዚህ በታች ያሉትን ግላዊ መረጃዎችን የሚመለከቱ ጥያቄዎች እንዲመልሱ እናበረታታዎታለን። ለማናቸውም ጥያቄ "ባልመልስ እመርጣለሁ" የሚለውን አማራጭ ሊመርጡ ይችላሉ።

ያጠናቀቁት ከፍተኛው የትምህርት ደረጃ ወይም ዲግሪ የትኛው ነው?

- ☐ አልተማርኩም
- ☐ ከሁለተኛ ደረጃ በታች
- ☐ የተወሰነ ሁለተኛ ደረጃ፣ ዲፕሎማ የለኝም
- ☐ የሁለተኛ ደረጃ ምሩቅ፣ GED ወይም ከዚህ እኩል የሆነውን ጨምሮ
- ☐ ቴክኒክ፣ ንግድ ወይም የሙያ ትምህርት ቤት
- ☐ የተወሰነ የቅድመ ምረቃ ትምህርት ወይም መለስተኛ ዲግሪ
- ☐ የመጀመርያ ዲግሪ
- ☐ የድህረ ምረቃ ድግሪ
- ☐ ባልመልስ እመርጣለሁ

አካል ጉዳት አለብዎት?

አካላዊ፣ አእምሯዊ እና/ወይም የእድገት ጉዳተኝነት ካለብዎት ወይም በዋና ዋና ተግባራት ላይ መሰረታዊ ውስንነት የሚያስከትል የጤና ችግር የአካል ጉዳት ወይም የጤና ችግር ሁኔታ ታሪክ ወይም ምዝገባ ካለበዎት አካል ጉዳት አለብዎት ተብለው ይታሰባሉ። ይህም አካል ጉዳተኛ ነዎት ተብለው የሚታሰቡ መሆን አለመሆንዎን ያካትታል።

☐ አዎ ☐ አይ ☐ ባልመልስ እመርጣለሁ

ጡረተኛ የሰራዊት አባልነት ወይም የወታደራዊ አገልግሎት ሁኔታዎ ምንድን ነው?

- ☐ እኔ የU.S. Armed Forces፣ Military Reserves ወይም National Guard ጡረተኛ ነኝ
- ☐ እኔ በአሁኑ ወቅታ ስራ ላይ ያለሁ የU.S. Armed Forces፣ Military Reserves ወይም የNational Guard አባል ነኝ
- ☐ ጡረተኛ የሠራዊት አባል አይደለሁም ወይም ወታደራዊ አገልግሎት የለኝም
- ☐ ባልመልስ እመርጣለሁ

ከሚከተሉት ውስጥ እርስዎን ከሁሉ የበለጠ የሚገልጽዎት የትኛው ነው? *ተገቢ የሆነውን ሁሉ ይምረጡ።*

- ☐ አሜሪካዊ ህንዳዊ፣ የአሜሪካ ተወላጅ ወይም የአላስካ ተወላጅ
- ☐ ኢስያዊ
- ☐ ጥቁር ወይም አፍሪካ አሜሪካዊ
- ☐ ሂስፓኒክ/ላቲኖ/ላቲና/ላቲንስ
- ☐ የሃዋይ ተወላጅ፣ ፓሲፊክ አይላንደር
- ☐ ነጭ
- ☐ መካከለኛው ምስራቅ/ሰሜን አፍሪካ
- ☐ ራሴን ልገልጽ እመርጣለሁ
- ☐ ባልመልስ እመርጣለሁ

እርስዎ ሂስፓኒክ፣ ላቲኖ፣ ላቲና፣ ላቲንስ ወይም ስፓኒሽ ነዎት? *ለጎድ መልስ ይምረጡ።*

- ☐ አዎ፣ እኔ ሂስፓኒክ፣ ላቲኖ/ላቲና/ላቲንስ ወይም ስፓኒሽ ነኝ
- ☐ አይ፣ እኔ ሂስፓኒክ፣ ላቲኖ/ላቲና/ላቲንስ ወይም ስፓኒሽ አይደለሁም
- ☐ ባልመልስ እመርጣለሁ
- ☐ እርግጠኛ አይደለሁም

ጾታዎ ምንድን ነው?

☐ ሴት ☐ ወንድ ☐ ባልመልስ እመርጣለሁ

የጾታ ለውጥ ያደረጉ ነዎት?

☐ አዎ ☐ ኣይ ☐ እየጠየቅኩ/እያጠናሁ ነው ☐ ባልመልስ እመርጣለሁ ☐ ይህ ጥያቄ ስለምን እንደሚጠይቅ አላውቅም

ስርዓተ ጾታዎ ምንድን ነው? *ተገቢ የሆነውን ሁሉ ይምረጡ*

☐ ስርዓተ ጾታ የለሽ ☐ ያልተጠቀሰ ሌላ ስርዓተ ጾታ

☐ ከሁለቱ ውጪ ☐ እየጠየቅኩ/እያጠናሁ ነው

☐ ሴት/ሴት ልጅ ☐ ባልመልስ እመርጣለሁ

☐ ወንድ/ወንድ ልጅ ☐ ይህ ጥያቄ ስለምን እንደሚጠይቅ አላውቅም

ወሲባዊ ዝንባሌዎን ወይም ጾታዊ ማንነትዎን እንዴት ይገልጹታል? *ተገቢ የሆነውን ሁሉ ይምረጡ*

☐ አሴክሹዋል ☐ ተመሳሳይ ስርዓተ ጾታ አፍቃሪ

☐ ባይክሹዋል ☐ ተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ

☐ ጌይ ☐ ስትሬይት (በዋናነት የምሳበው ወደ ሌላው ጾታ ወይም ስርዓተ ጾታ ነው)

☐ ሌዝቢያን ☐ ያልተጠቀሰ ሌላ ወሲባዊ ዝንባሌ

☐ ፓንክሹዋል ☐ ባልመልስ እመርጣለሁ

☐ ኩዌር ☐ ይህ ጥያቄ ስለምን እንደሚጠይቅ አላውቅም

☐ እየጠየቅኩ/እያጠናሁ ነው

ማረጋገጫ

እባክዎ የጥቅማ ጥቅም ማመልከቻዎን ከማስገባትዎ በፊት የሚከተለውን ማረጋገጫ ያንብቡ።

1. እኔ የ ዩናይትድ ስቴተትስ ዜጋ መሆኔን ወይም የጥቅማ ጥቅም ክፍያ በጠየቅኩበት ሳምንት ውስጥ ዩናይትድ ስቴተትስ ውስጥ እንድሰራ በህጉ መሰረት የተፈቀደልኝ መሆኑን አረጋግጣለሁ።
2. የተጠየቅኳቸውን ጥያቄዎች ተረድቻቸዋለሁ። የሰጠሁት መልስ እኔ እስከማውቀው ድረስ እውነት ነው።
3. በስራ አጥ የመድን ዋስትና ፕሮግራም ስር የስራ አጥ የመድን ዋስትና ጥቅማ ጥቅም ለማግኘት የህሰት ማረጋገጫ መስጠት እንደሚያስቀጣ በህጉ የተደነገገ መሆኑን ተረድቻለሁ።
4. የስራ አጥ የመድን ዋስትና ጥቅም ክፍያ ኦንላይን ወይም በተች-ቶን ስልክ በምጠይቅበት ጊዜ፣ለግላዊ የመለያ ቁጥሬ (PIN) ደህንነት ኃላፊነት እወስዳለሁ። የኔን PIN ከረሳሁት ወይም በሌላ ሰው የታወቀ ከሆነ PIN ለማስቀየር ለኦሬጎን ስራ መምሪያ አሳውቃለሁ።
5. ይህን ማመልከቻ በመቅረብ፣ በዚህ ሰነድ መሰረት ለስራ የተመዘገብኩ ሲሆን ሊከፈሉኝ ለሚችሉ ጥቅማ ጥቅሞች የመጀመርያው ውሳኔ እንዲወሰንልኝ እጠይቃለሁ። የኦሬጎን ስራ መምሪያ ለስራ አጥ የመድን ዋስትና አስተዳደር እና ለስራ ቅጥር አገልግሎት ተግባራት እኔ የሰጠሁትን መረጃ ከማናቸውም ምንጭ እንዲያገኝ እና እንዲጠቀምበት ፈቅጀለታለሁ።
6. **የብቁነት ማሳወቂያ: የርስዎ የስራ ፍለጋ መስፈርቶች**

   በሚፈለገው መልኩ ስራ አለመፈለግ ጥቅማ ጥቅም ያስከለክላል።

   የጥቅማ ጥቅም ክፍያ ለሚጠይቁበት ለያንዳንዱ ሳምንት፣ የሚከተሉትን መፈጸም አለብዎት፡

   - ስራ ለመስራት አካላዊ እና አእምሯ ችሎታ ሊኖርዎት ይገባል
   - ለሙሉ ሰዓት፣ የትርፍ ሰዐት እና ጊዜያዊ ስራ መገኘት መቻል አለብዎት - አብዛኛውን ጊዜ ለርስዎ የስራ ዓይነት መደበኛ በሆኑ ቀናት እና ሰዓታት
   - ሊቀጠሩባቸው የሚችሏቸውን ስራዎች በንቃት መፈለግ

ስራ በንቃት እየፈለጉ ነው ተብለው እንዲታሰቡ፣ ክፍያ በሚጠይቁበት በያንዳንዱ ሳምንት ከአሰሪዎች ጋር ሁለት ቀጥተኛ ግኝኙነቶች ማድረግ እና ሶስት ተጨማሪ የስራ ፍለጋ እንቅስቃሴዎች ማድረግ አለብዎት። ስለ ስራ ለመጠየቅ ወይም አሰሪው በሚመርጠው መልኩ ለስራ ለማመልከት ከአሰሪዎች ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ማድረግ አለብዎት።

የሚከተሉትን መመዝገብ አለብዎት፡

- ግንኙነት ያደረጉበትን ቀን
- የኩባንያውን ስም፣ ስልክ ቁጥር እና አድራሻ ወይም ኦንላይን ስራ የተለጠፈበት የመለያ ቁጥር
- ያናገሩትን ሰው (ከተቻለ)
- ከኩባንያው ጋር የተገናኙበት መንገድ (ስልክ፣ ሲቪ፣ ኦንላይን የገባ ማመልከቻ፣ ኢሜይል፣ ወዘተ.)
- ያመለከቱበትን የስራ አይነት ወይም የስራ መደብ
- ግንኙነትዎ ያመጣው ውጤት (አመልክቻለሁ፣ ተቀጥሬያለሁ፣ አልተቀጠርኩም፣ ቃለ መጠይቅ፣ መልስ የለም፣ ወዘተ.)

ተጨማሪ የስራ ፍለጋ እንቅስቃሴዎችዎ ከአሰሪ ጋር የተደረጉ ተጨማሪ ግንኙነቶችን፣ ሲቪ ማሻሻልን ወይም የወጡ የስራ ዝርዝሮችን ማየትን ሊያካትቱ ይችላሉ። ቀኑን እና የፈጸሙትን ተግባር በቅደም ተከተል ያቅርቡ።

የሚከተሉት ሁኔታዎች የተለመዱ አይደሉም፡

እርስዎ ከማህበሩ ውጪ የሆነ ስራ እንዲፈልጉ የማይፈቅድልዎ የስምሪት ማህበር ውስጥ በጥሩ አቋም ላይ ያሉ የማህበር አባል ከሆኑ፣ ከማህበሩ ውጪ በሆነ የስራ ዝርዝር ላይ ከቆዩ፣ ከማህበሩ ጋር እየተገናኙ ከቀጠሉ እና በማህበሩ ሲላኩ ስራ መቀበል እና ሪፖርት ማድረግ የሚችሉ ከሆነ ስራ በንቃት እየፈለጉ ነዎት።

ከተቀነሱ ወይም የስራ ሰዓትዎ ከተቀነሰ እና ወደዚያው አሰሪ ተመልሰው ስራ እንደሚሰሩ የሚጠብቁ ከሆነ ጊዜያዊ ስራ አጥ ሊሆኑ ይችላሉ። ወደ ሙሉ ሰዓት ስራ መመለስ ወይም ከሳምንታዊ የጥቅማ ጥቅም መጠን በላይ ክፍያ የሚያስገኝ ስራ መስራት አለብዎት።
የሙሉ ሰዓት ስራ ከሰሩበት ወይም ከሳምንታዊ የጥቅማ ጥቅም መጠን በላይ የሆነ ገቢ ካገኙበት ቀን ጀምሮ ከአራት ሳምንት የበለጠ ጊዜ መኖር የለበትም።

□ ከላይ ባሉት ማረጋገጫዎች እስማማለሁ

ፊርማ:	ቀን:

ለእርስዎ ሊያውቁት የሚገባ አስፈላጊ መረጃ

የክፍያ ጥያቄዎ አንዴ ከታየ በኋላ፣ ሳምንታዊ የክፍያ ጥያቄዎችን ማቅረብን፣ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ በድጋሚ ክፍያ መጠየቅን፣ የክፍያ ሁኔታዎን ማየትን፣ አድራሻዎን መቀየርን እና በኤሌክትሮኒክ ተቀማጭ ለመጠቀም መመዝገብን ጨምሮ በርካታ የክፍያ ተግባራትን ለመፈጸም Frances Online ከሁሉም በላይ በጣም ፈጣን የሆነው መንገድ ነው። ወደዚህ ድረገጽ ይሂዱ: frances.oregon.gov

የሥራ አጥ ክፍያ መረጃዎች ሚስጥራዊ ናቸው። እርስዎ ግለሰቡ በርስዎ ስም ጥያቄዎችን እንዲያቀርብ እና መረጃ እንድንሰጥ የሚፈቅድ የተፈረመ ማረጋገጫ ካልሰጡን በስተቀር ስለርስዎ ክፍያ መረጃ ለሚጠይቀን ለማናቸውም ሰው መረጃ አንሰጥም።

ቀጥሎስ ምን ይደረጋል?

ማድረግ ያለብዎት ይሄንን ነው።

ስራ አጥ ለሆኑበት ለማንኛውም ሳምንት ጥቅማ ጥቅም እንዲከፈልዎ ይጠይቁ። ሳምንቱ የሚጀምረው እሁድ ሲሆን የሚያበቃው ቅዳሜ ነው። ጥያቄውን ያቀረቡበት የመጀመርያው ሳምንት መጠባበቂያ ሳምንት ይባላል። ለዚህ ሳምንት ክፍያ አያገኙም፣ ነገር ግን የወደፊት ክፍያዎችን ለማግኘት ክፍያውን መጠየቅ አለብዎት። የመጀመርያውን የክፍያ ጥያቄ ማቅረብ ብቻውን የመጠባበቂያ ሳምንት ስንቅ ማግኘትን አያረጋግጥም። ለመጠባበቂያ ሳምንቱ እንደ ማናቸውም ሌላ ሳምንት የክፍያ ጥያቄ መቅረብ አለበት።

Weekly claimዎን በFrances Online ላይ ማስገባት ይችላሉ። ጥያቄውን ለማቅረብ በጣም ፈጣን የሆነ መንገድ ነው። ስርዓቱ ስለ ክፍያ ጥያቄዎ በርካታ የክፍያ ተግባራት ማከናወን ይችላል። በተጨማሪም ስልክ በመጠቀም የክፍያ ጥያቄዎን ማቅረብ ይችላሉ። የክፍያ ጠያቂ የመረጃ ሰነድ ይሄንን እንዴት ሊያደርጉ እንደሚችሉ ይገልጽልዎታል።

iMatchSkills ላይ መመዝገብ እና ከWorkSource Center ባልደረባ ጋር ግላዊ ቃለመጠይቅ ማድረግ ይኖርብዎታል። iMatchSkills እርስዎን ከቀጣሪዎች እና አሰሪዎች ጋር የሚያገናኝ የኦሬጎን የስራ መምሪያ እንድ መሳርያ ነው። እንዴት መመዝገብ እና ግምገማዎን ማጠናቀቅ እንደሚችሉ የሚነግርዎ አንድ ደብዳቤ በጥቂት ቀናት ውስጥ ይደርስዎታል። ምዝገባዎትን እና ግላዊ ግምገማዎን አለማጠናቀቅ ጥቅማ ጥቅምዎን እንዲከለከሉ ያስደርግዎታል።

እኛ የምናደርገው ይህንን ነው።

የኛ የክፍያ ባልደረቦች የእርስዎ የስራ አጥ የክፍያ ጥያቄ ከመወሰኑ በፊት እርስዎ ያቀረቡትን መረጃ ይገመግማሉ። ይህ ሂደት ጥቂት ቀናት ሊወሰድ ይችላል። ተጨማሪ መረጃ ከፈለግን እናናግርዎታለን። የርስዎን ሳምንታዊ የጥቅማ ጥቅም መጠን የሚጠቁም መግለጫ በፖስታ እንልካለን። የርሰዎን ጥቅማ ጥቅም ለመወሰን ጥቅም ላይ የዋሉትን ደመወዞች ይዘረዝራል። ከግዛት እና ከፌደራል ኤጀንሲ ውጪ ሊኖርዎ የሚችሉ ማናቸውንም ደመወዞች እንጠይቃለን። እነዚህም ለኛ ኤጀንሲ ሲደርሱ በክፍያዎ ላይ እንደምራቸዋለን።

የመጀመርያው የጥቅማ ጥቅም ክፍያዎ በቼክ የሚከፈል ሲሆን ቀጣዮቹ ክፍያዎች በኤሌክትሮኒክ የክፍያ ዘዴ በReliaCard® VISA ወይም በቀጥታ ተቀማጭ የሚከፈሉ ይሆናል። ክፍያዎችን የሚመለከቱ ተጨማሪ ዝርዝር መረጃዎች የክፍያ ጥያቄዎ ከታየ በኋላ ሊገኙ ይችላሉ።

እርዳታ ይፈልጋሉ?

ይህ መረጃ አስፈላጊ ነው። የኦሬጎን የቅጥር መምሪያ (The Oregon Employment Department, OED) የእኩል እድል ኤጀንሲ ነው። አገልግሎቶቻችንን መጠቀም እንዲችሉ OED ነፃ እገዛን ይሰጣል። አንዳንድ ምሳሌዎች የምልክት ቋንቋ እና የንግግር ቋንቋ አስተርጓሚዎች፣ በሌሎች ቋንቋዎች የተጻፉ ጽሑፎች፣ ትልቅ ህትመት፣ ኦዲዮ እና ሌሎች ቅርጸቶች ናቸው። እገዛ ለማግኘት፣ እባክዎ ወደ unemployment.oregon.gov/am ይሂዱ እና ያግኙን ቅጽ የሚለውን ጠቅ ያድርጉ ወይም በ 877-345-3484 ይደውሉልን። የTTY ተጠቃሚዎች 711 ይደውላሉ።

እባክዎ የተሞላ ማመልከቻዎን በፖስታ ወይም በፋክስ ለሚከተለው ያስገቡ:

ፖስታ: Oregon Employment Department | P. O. Box 14135 | Salem, OR 97309-5068

ፋክስ: 866-345-1878

U.S. Bank ReliaCard® ቅድመ-ግኝት ይፋ ማድረግ
የፕሮግራሙ ስም፡- Oregon Unemployment Insurance

አንዳንድ ቁሳቁሶች እና አገልግሎቶች በእንግሊዝኛ ብቻ ሊገኙ ይችላሉ። በዚህ ግንኙነት ውስጥ ያሉት አገናኞች ወደ እንግሊዝኛ ቋንቋ ድረ-ገጾች ሊመሩዎት ይችላሉ።

ክፍያዎችዎን እንዴት እንደሚቀበሉ አማራጮች አሉዎት፣
በቀጥታ ወደ ባንክ ሒሳብዎ ወይም ወደዚህ ቅድመ ክፍያ ካርድ ማስገባትን ጨምሮ።
ያሉትን አማራጮች ኤጀንሲዎን ይጠይቁ እና አማራጭዎን ይምረጡ።

ወርሃዊ ክፍያ	በአንድ ግዢ	በኤቲኤም ማውጣት	ጥሬ ገንዘብ እንደገና መጫን
$0	**$0**	**$0** በአውታረ መረብ ውስጥ **$2.00*** ከአውታረ መረብ ውጪ	**N/A**

የኤቲኤም ሂሳብ ጥያቄ (በአውታረ መረብ ውስጥ ወይም ከአውታረ መረብ ውጪ)	$0
የደንበኞች አገልግሎት (በራስ ሰር ወይም ቀጥታ ወኪል)	$0 በአንድ ጥሪ
እንቅስቃሴ-አልባነት (ያለምንም ግብይት ከቆዩ ከ365 ቀናት በኋላ)	$2.00 በወር

ሌሎች 3 አይነት ክፍያዎችን እናስከፍላለን።

* ይህ ካርድ እንዴት እና የት ጥቅም ላይ እንደሚውል ላይ በመመስረት ይህ ክፍያ ዝቅተኛ ሊሆን ይችላል።

የገንዘብዎን እና ቀሪ ሂሳብዎን መረጃ ለማግኘት ነፃ መንገዶችን ለማግኘት ከዚህ ጋር የተያያዘውን የክፍያ መርሃ ግብር ይመልከቱ።

ምንም ትርፍ ገንዘብ የመውሰድ/የብድር ባህሪይ የለም።
የእርስዎ ገንዘቦች ለFDIC መድን ብቁ ናቸው።

ስለቅድመ ክፍያ ሂሳቦች አጠቃላይ መረጃ ለማግኘት *cfpb.gov/prepaid* ይጎብኙ።
በካርድ ጥቅል ውስጥ ላሉ ሁሉም ክፍያዎች እና አገልግሎቶች ዝርዝሮችን እና ሁኔታዎችን ያግኙ ወይም ወደ **1-855-279-1270** ይደውሉ ወይም **usbankreliacard.com** ይጎብኙ።

የU.S. Bank ReliaCard® የክፍያ መርሃ ግብር
የፕሮግራሙ ስም፡- የOregon Unemployment Insurance (የኦሪገን የሥራ አጥነት መድን)

ሁሉም ክፍያዎች	መጠን	ዝርዝሮች
ጥሬ ገንዘብ ያግኙ		
የኤቲኤም ማውጣት (በአውታረ መረብ ውስጥ)	$0	ይህ በእያንዳንዱ የገንዘብ ማውጣት የምናስከፍለው ክፍያ ነው። “አውታረ መረብ ውስጥ” የሚለው የU.S. Bank ወይም የMoneyPass® ኤቲኤም አውታረ መረቦችን ያመለክታል። ቦታዎች *usbank.com/locations* ወይም *moneypass.com/atm-locator.html* ላይ ይገኛሉ።
የኤቲኤም ማውጣት (ከአውታረ መረብ ውጪ)	$2.00	ይህ በእያንዳንዱ የገንዘብ ማውጣት የምናስከፍለው ክፍያ ነው። ይህ ክፍያ በወር ለመጀመሪያዎቹ ሁለት የATM ገንዘብ ማውጣቶች ነጻ ይደረጋል፣ ይህም ሁለቱንም የኤቲኤም ገንዘብ ማውጣትን (ከአውታረ መረብ ውጪ) እና ዓለም አቀፍ የኤቲኤም ገንዘብ ማውጣትን ያካትታል። "ከአውታረ መረብ ውጪ" የሚለው ከU.S. Bank ወይም ከMoneyPass የኤቲኤም አውታረ መረቦች ውጪ ያሉትን ሁሉንም ኤቲኤሞች ያመለክታል። ግብይቱን ባይጨርሱም እንኳ በኤቲኤም ከዋኙ ክፍያ እንዲከፍሉ ሊደረጉ ይችላሉ።
በባንክ ሰራተኛ እገዛ ጥሬ ገንዘብ ማውጣት	$0	ይህ Visa® በሚቀበል በባንክ ወይም በብድር ማኅበር (ክሬዲት ዩኒየን) ያለ የባንክ ሰራተኛ አማካኝነት ጥሬ ገንዘብ ከካርድዎ ሲያወጡ የምናስከፍለው ክፍያ ነው።
ካርድዎን ከዩናይትድ ስቴትስ ውጪ መጠቀም		
ዓለም አቀፍ ግብይት	3%	ይህ ከውጪ ነጋዴዎች ግዢ ለመፈጸም እና ከውጪ ኤቲኤሞች ገንዘብ ለማውጣት ካርድዎን ሲጠቀሙ እኛ የምናስከፍለው ነው እንዲሁም ከማንኛውም ምንዛሪ ቅያሬ በኋላ የግብይት የዶላር መጠኑ መቶኛ ነው። አንዳንድ ግብይቶች፣ እርስዎ እና/ወይም ነጋዴው ወይም ኤቲኤም በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ቢሆኑም እንኳ፣ በሚመለከተው የአውታረ መረብ ህግ መሰረት እንደ የውጭ ግብይቶች ይቆጠራሉ እና እነዚህ ነጋዴዎች፣ ኤቲኤሞች እና ግብይቶች ለዚህ ዓላማ እንዴት እንደሚመደቡ አንቆጣጠርም።
ዓለም አቀፍ ከኤቲኤም ገንዘብ ማውጣት	$2.00	ይህ በእያንዳንዱ የገንዘብ ማውጣት የምናስከፍለው ክፍያ ነው። ይህ ክፍያ በወር ለመጀመሪያዎቹ ሁለት የATM ገንዘብ ማውጣቶች ነጻ ይደረጋል፣ ይህም ሁለቱንም የኤቲኤም ገንዘብ ማውጣትን (ከአውታረ መረብ ውጪ) እና ዓለም አቀፍ የኤቲኤም ገንዘብ ማውጣትን ያካትታል። ግብይቱን ባያጠናቅቁም እንኳ በኤቲኤም ከዋኙ አማካኝነት ክፍያ እንዲከፍሉ ሊደረጉ ይችላሉ።
ሌላ		
የካርድ መተካት	$0	ይህ ወደ እርስዎ በፖስታ ለተላከ ለአንድ የካርድ መተካት ከመደበኛ ማድረስ ጋር (እስከ 10 የስራ ቀናት የሚወስድ) የምናስከፍልዎት ክፍያ ነው።
የካርድ መተካት የተፋጠነ ማድረስ	$15.00	ይህ ከማንኛውም የካርድ መተካት ክፍያ በተጨማሪ ለተፋጠነ ማድረስ (እስከ 3 የስራ ቀናት የሚወስድ) የምናስከፍልዎት ክፍያ ነው።
እንቅስቃሴ-አልባነት	$2.00	በካርድዎ ምንም ዓይነት ግብይት ሳያከናውኑ ወይም ካርዱ ላይ ገንዘብ ሳይጫን 365 ተከታታይ ቀናት ካለፉ በኋላ፣ በየወሩ የምናስከፍለው ክፍያ ነው። ይህ ክፍያ በሕግ የተከለከለበት ቦታ አይጠየቅም።

ይህ ግንኙነት የሚቀርበው በአማርኛ ቢሆንም፣ የU.S. Bank ግንኙነቶችን እና ከውል ስምምነቶችዎ ጋር የተያያዙ

ReliaCard ከVisa U.S.A. Inc. © 2026 U.S. Bank ለተገኘ ፈቃድ በመገዛት በU.S. Bank National Association የተሰጠ ነው። Member FDIC።

ሰነዶችን፣ ይፋ ማድረግን፣ ማስታወቂያዎችን እና መግለጫዎች፣ የበይነ መረብ እና የሞባይል ባንክ አገልግሎቶች እና የተገናኙ ይዘቶችን ተከትሎ በእንግሊዝኛ ብቻ ሊገኙ ይችላሉ። ይህንን ምርት ወይም አገልግሎት ለመረዳት እና ለመጠቀም እነዚህን ሰነዶች ማንበብ እና መረዳት መቻል ወይም በመተርጎም ላይ እገዛ ሊያገኙ ይገባል። የእንግሊዝኛ ሰነዶችን በመጠየቅ ማግኘት ይቻላል።

የእርስዎ ገንዘቦች ለFDIC መድን ብቁ ናቸው። ገንዘብዎ የFDIC ዋስትና ባለው ተቋም፣ በU.S. Bank National Association ውስጥ የሚቀመጥ ሲሆን፣ U.S. Bank ቢከስር፣ ወይም አገልግሎት መስጠት ቢያቋርጥ በFDIC እስከ $250,000 ዶላር ድረስ ዋስትና ይኖረዋል። ለዝርዝሮች ***fdic.gov/deposit/deposits/prepaid.html*** ይመልከቱ።

ምንም ትርፍ ገንዘብ የመውሰድ/የብድር ባህሪይ የለም።
በስልክ **1-855-279-1270** በመደወል፣ በፖስታ ሳጥን 551617፣ Jacksonville, FL 32255 በፖስታ በመላክ ወይም ***usbankreliacard dot com*** በመጎብኘት Cardholder Services (የደንበኛ አገልግሎቶችን) ያግኙ።

ስለቅድመ ክፍያ ሂሳቦች አጠቃላይ መረጃ ለማግኘት *cfpb.gov/prepaid* ይጎብኙ። ስለቅድመ ክፍያ መለያ ቅሬታ ካልዎት፣ ወደ የደንበኛ ፋይናንሺያል ጥበቃ ቢሮ (Consumer Financial Protection Bureau) 1-855-411-2372 ላይ ይደውሉ ወይም *cfpb.gov/complaint* ይጎብኙ።

CR-68221224 - Amharic

ReliaCard ከVisa U.S.A. Inc. © 2026 U.S. Bank ለተገኘ ፈቃድ በመገዛት በU.S. Bank National Association የተሰጠ ነው። Member FDIC።

English – If you require this document to be read digitally for accessibility in additional languages, please contact Cardholder Services to utilize the language line at the number on the back of your card.

Amharic - ይህ ሰነድ በተጨማሪ ቋንቋዎች ለማግኘት በዲጂታላዊ አግባብ እንዲነበብ ከፈለጉ፣ እባክዎ በካርድዎ ጀርባ ባለው ቁጥር ላይ ያለውን የቋንቋ መስመር ለመጠቀም የካርድ ባለቤት አገልግሎቶችን ያግኙ።

Arabic- إذا كنت تريد قراءة هذا المستند رقميًا لإمكانية الوصول إليه بلغات إضافية، فيرجى الاتصال بخدمات حاملي البطاقات لاستخدام سطر اللغة على الرقم الموجود على ظهر بطاقتك

Chinese - **如需以其他**语言进行数字化方式阅读本文档来提高无障碍性，请首先与持卡人服务联系，以使用卡背面语言支援服务号码。

Chinese Traditional - **如果您因無障礙訪問需求而需要本文檔用其他語種以數位方式朗讀，請撥打卡片背面號碼聯絡持卡人服務部，以便使用語言專綫。.**

Farsi - اگر جهت دسترسی به دیگر زبان‌ها، نیاز دارید که این سند به صورت دیجیتالی خوانده شود، لطفاً با Cardholder Services تماس بگیرید تا از خط زبان در شماره پشت کارت خود استفاده نمایید.

Korean - 다른 언어로 접근성을 높이기 위해 이 문서를 디지털 방식으로 읽어야 하는 경우, 뒷면에 있는 번호로 카드소지자 서비스에 문의하여 번역 서비스를 이용하시기 바랍니다.

Laotian - ຖ້າວ່າທ່ານຕ້ອງການໃຫ້ເອກະສານນີ້ຖືກອ່ານແບບດິຈິຕອລ ເພື່ອເຂົ້າເຖິງພາສາເພີ່ມຕື່ມ, ກະລຸນາຕິດຕໍ່ບໍລິການຜູ້ຖືບັດເພື່ອນຳໃຊ້ສາຍພາສາຕາມຕົວເລກທີ່ຢູ່ທາງດ້ານຫຼັງຂອງບັດຂອງທ່ານ.

Russian - Чтобы прослушать этот документ на другом языке в цифровом формате, обратитесь на языковую линию, позвонив в Cardholder Services по номеру, указанному на обратной стороне вашей карты.

Somali - Haddii aad u baahan tahay dukumeentigan in si dhijitaal ah loogu akhriyo si loogu helo luuqado dheeraad ah, fadlan kala xidhiidh Adeegyada Kaar-haystaha (Cardholder services) lambarka ku yaala dhabarka kaadhkaaga si aad uga faa'iidaysato laynka luuqada.

Vietnamese - Nếu bạn muốn tài liệu này được đọc dưới dạng kỹ thuật số để có thể truy cập bằng các ngôn ngữ khác, vui lòng liên hệ với Dịch vụ dành cho chủ thẻ để sử dụng đường dây ngôn ngữ theo số điện thoại ở mặt sau thẻ của bạn.